# <u>የትግል ደላላ</u>

ጠኋት ፣ ዓለም አቀፍ ፣ ሲረፍድ ፣ አህጉራዊ
ሲመሻሽ ፣ ደርሰው ፣ የጎጥ ፣ ባህታዊ
እምነት ፣ ጽናት ፣ የለሽ ፣ ወላዋይ ፣ ሃሳዊ
ወይ ፣ ለነፍስ አይሰሩ ፣ ወይም ፣ ለምድራዊ
የትግል ፣ አመንዝራ ፣ ሁልጊዜ ዘማዊ ።

በትግል ፣ ማመንዘር ! በአቋም ፣ ማመንዘር !
አንዴ ፣ ሁሉን አቀፍ ፣ አንዴ ፣ በጎጥ መንደር
ጥልቅ ፣ አንደ እርጎ ዝንብ ፣ እንዳሻ ማዳከር
ይሉኝታን አያውቁ ፣ የለባቸው ማፈር
ለመታወቅ ብቻ ፣ መዳከር መፍጨርጨር
ቃላት በማጣፊጥ ፣ በባዶ መፌከር
ስም እየቀየሩ ፣ ሰውን ማደናገር
ለገንጣይ ፣ ለጠባብ ፣ አንገትን ማቀርቀር ።

ባቋሙ ያልጸና ፣ ወላዋይ ሾለካ
ጎጠኛው ወርዶልን ፣ ጎጠኛን ሊተካ
ከዚያች ከወስላታም ፣ ተንጎዳጉዳል ለካ
ሊያጠፋልን ጭራሽ ፣ የኢትዮጵያን ዱካ
እንደ መልካም ዜና ፣ በአሰልቺ ሰበካ
ዘንድሮም እንዳምናው ፣ ተይዟል ትረካ
የአሁኑ ይባስ ፣ መጣ ፣ ይሄም አለ ለካ
አስር ቦታ እረጋጭ ፣ የወሬ ፋብሪካ
የማያውቁበትን ፣ ምናል ባይነካ ። ?

እዚም ፣ እዚያም መሮጥ ፣ ሁሉምጋ መዳከር
አቋም ፣ ጽናት ፣ ሳይኖር ፣ በባዶ ማጋፈር
አገርና ህዝብን ፣ አዋርዶ ማሳፈር
የትግል ደላላ ፣ ፒምፕ ፣ አትሻም አገር ።

ታዛቢው ... October 10, 2010